# JESUS 316

## ኢየሱስ ማን ነው?

**ኢየሱስ ማን ነው?** መጽሐፍ ቅዱስ ለዚህ ጥያቄ ብቸኛውን ትክክለኛ መልስ ይሰጠናል። ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ሲል ፅፏል፣ *«ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው ናቸው፤»* 2ኛ ጢሞ 3፥16። የእግዚአብሔር እስትንፋስ ያለበት መጽሐፍ ቅዱስ፣ ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ፣ ኢየሱስ ከዘላለም እስከ ለዘላለም አምላክ እንደሆነ ያስተምራል። መጽሐፍ ቅዱስ *«ያለውና የነበረው የሚመጣውም አልፋና ዖሜጋ»* መሆኑን ራዕይ 1፥8 ይናገራል። መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስን እንደ አምላክ፣ ፈጣሪ፣ ታላቅ እረኛ፣ ጌታ፣ ቤዛ፣ የእግዚአብሔር በግ፣ የጌቶች ጌታ፣ የነገሥታት ንጉሥ፣ አማኑኤል (ማለትም እግዚአብሔር ከእኛ ጋር)፣ አዳኝ፣ ሊቀ ካህናት እና ትንሳኤና ሕይወት እንደሆነ ይገልፃል።

**ኢየሱስ ፈጣሪ ነበር።** *«በመጀመሪያ ቃል ነበረ፤ ቃልም ከእግዚአብሔር ጋራ ነበረ፤ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። ሁሉ ነገር በርሱ ተፈጥሯል፤ ቃልም ሥጋ ሆነ፤ በመካከላችንም ዐደረ፤ እኛም ጸጋንና እውነትን ተሞልቶ ከአባቱ ዘንድ የመጣውን የአንድያ ልጅን ክብር አየን።»* ከዮሐንስ 1፥1-14 የተወሰደ። *«ሁሉ ነገር በርሱ ተፈጥሯል፤ በሰማይና በምድር ያሉ፣ የሚታዩና የማይታዩ፣ ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ኀይላት፣ ገዦች ቢሆኑ ወይም ባለሥልጣናት፣ ሁሉም ነገር በርሱና ለርሱ ተፈጥሯል። እርሱ ከሁሉ በፊት ነው፤»* ከቆላስይስ 1፥16-17 የተወሰደ።

**ኢየሱስ «እኔ» ያለው ነው።** ከዘጸአት 3 (በ1,450 ዓዓ) የጌታ መልአክ ተብሎ የተጠራው ኢየሱስ ሙሴን ጠርቶ ራሱን እንደ ታላቁ *«እኔ»* ገለጸ። በዮሐንስ 8፣ ኢየሱስ ከአብርሃም በፊት (በ2,100 ዓዓ ገደማ) እና ከአይሁድ ሕዝብ በፊት የነበረው ታላቅ «እኔ» ብሎ ራሱን አወጀ። አይሁዶች ኢየሱስ አምላክነቱን እንዳወጀ በማየታቸው ሊገድሉት ድንጋይ አነሱ። በኋላም ኢየሱስ *«እኔና አብ አንድ ነን።»* ዮሐንስ 10፥30-31 ብሎ ተናግሯል። አይሁድም እንደ ገና ድንጋዮችን አነሡ።

**ኢየሱስ በብሉይ ኪዳን ውስጥ አለ።** ማንም አብን አይቶት አያውቅም፣ ዮሐንስ 1፥18፣ 6፥46። ይሁንና፣ እግዚአብሔር ቅድመ-በስጋ የተገለጠው ኢየሱስ በቤተልሔም ከመወለዱ በፊት በብሉይ ኪዳን ዘመን ለበርካታ ሰዎች ተገለጠ። በዘፍጥረት 16 እና 21 ላይ የእግዚአብሔር መልአክ ሆኖ ለአጋር፣ በዘጸአት 3 ለሙሴ፣ በመሳፍንት 6 ለጌዴዎን እና በመሳፍንት 13 ለሳምሶን ወላጆች ተገለጠ። ኢየሱስ በዘፍጥረት 18 እና 22 ለያዕቆብ፣ ድጋሚም በዘፍጥረት 31 እና 32 ተገለጠለት። ኢሳ 48፥12-19 (በ700 ዓዓ ገደማ የተጻፈ) ኢየሱስን በሥላሴ ውስጥ እንደ አንዱ ጠቅሷል።

**በትንቢት የተነገረለት ኢየሱስ ነበር።** ከመቶ ዓመታት በፊት የተተነበዩ ከ300 በላይ የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች የኢየሱስን ልደት፣ ሕይወትና ሞት ይገልጻሉ። በመዝሙር 22 ላይ ከተነገሩት ትንቢቶች መካከል አንዳንዶቹ ስለ ስቅለቱ አሰቃቂ መግለጫ ይሰጣሉ (በ1,000 ዓዓ በድንጋይ መወገር የግድያ ዘዴ በነበረበት ጊዜ የተጻፈ)። የመዝሙር 22 ትንቢቶች ፍጻሜ በማቴዎስ 27 ላይ ተመዝግቧል።

**ኢየሱስ ፍፁም አምላክ ፍጹም ሰው ሆነ።** ነቢዩ ኢሳይያስ *«ሕፃን ተወልዶልናል፤ወንድ ልጅም ተሰጥቶናል፤»* ኢሳይያስ 9፥6 ሲል ተንብዮአል። ኢየሱስ ኃያል አምላክ መሆኑን ኢሳይያስ ገልጿል። ዘላለማዊው ልጅ በቤተልሔም ተወለደ። ኢየሱስ ከመወለዱም በፊት ከዘላለም በፊት ነበረ። «የእግዚአብሔር ልጅ» የሚለው የማዕረግ ስም መወለድን ሳይሆን ስፍራውን ይገልጻል። በቤተልሔም መወለዱ ህልውናው በዚያ ጀመረ ማለት አይደለም። ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፏል፡- *«በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረው ያ አስተሳሰብ፣ በእናንተም ዘንድ ይሁን፤ እርሱ በባሕርዩ አምላክ ሆኖ ሳለ፣ ከእግዚአብሔር ጋራ መተካከልን ሊለቅቀው እንደማይገባ አድርጎ አልቈጠረውም፤ ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ፣ ሰውም አምሳል ተገኝቶ፣ ራሱን ባዶ አደረገ፤ ሰው ሆኖ ተገልጦም፣ ራሱን ዝቅ አደረገ፤ እስከ ሞት፣ ያውም በመስቀል ላይ እስከ መሞት ድረስ ታዛዥ ሆነ።»* ፊልጵስዩስ 2፥5-8። ኢየሱስ አምላክ ሆኖ ሳለ ፍፁም ሰው ሆነ። ዘላለማዊው፣ ቀድሞም የነበረው ኢየሱስ ሰው ለመሆን ከሰማይ ወረደ፣ ዮሐንስ 3፥13፣ 31፣ ዮሐንስ 6፥33-38። ኢየሱስ በአንድ ጊዜ ፍፁም አምላክና ሰው ነበር።

**ኢየሱስ ተአምራትን አድርጓል።** ብዙዎቹ ተአምራቱም በአዲስ ኪዳን ውስጥ ይገኛሉ። ሶስት አስደናቂ ክስተቶች የእርሱን አዋጅ ደግፈዋል። በተአምር 5,000 ሰዎችን መገበ ከዚያም *«የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤»* ዮሐንስ 6፥35 አለ *«በዓለም ሳለሁ የዓለም ብርሃን እኔ ነኝ።»* ዮሐ 9፥1-8። ካለ ኋላ ዓይነ ስውራንን ፈውሷል። እንዲህም አለ *«ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፤ በእኔ የሚያምን ቢሞት እንኳ በሕይወት ይኖራል፤»* ዮሐንስ 11፥25። ከዚያም ኢየሱስ ለአራት ቀናት ሞቶ ወደነበረው የወዳጁ አልዓዛር መቃብር ሄዶ ከሞት አስነሳው። ኢየሱስ ህሙማንን፣ ሽባዎችን፣ ደንቆሮዎችን፣ ዲዳዎችን፣ ለምጻሞችን እና በሽተኞችን ፈውሷል። ውሃውን ወደ ወይን ጠጅ ቀይረ፤ በውሃ ላይ ተራመደ እና ባሕሩን ጸጥ አደረገ። ማቴዎስ 9፥2-7 *«በዚያም ሰዎች አንድ ሽባ ሰው በቃሬዛ ተሸክመው ወደ እርሱ አመጡ።*

ኢየሱስም እምነታቸውን አይቶ ሽባውን፣ *«አይዞህ አንተ ልጅ፤ ኀጢአትህ ተሰርዮልሃል»* አለው። በዚህ ጊዜ የአይሁድ ሃይማኖት መምህራን፣ *«ይህማ እግዚአብሔርን መሳደብ ነው»* በማለት በልባቸው አጕረመረሙ። ኢየሱስ ሐሳባቸውን ተረድቶ እንዲህ አለ፤ *"ክፉ ነገር በልባችሁ ለምን ታስባላችሁ? ለመሆኑ፣ 'ኀጢአትህ ተሰርዮልሃል' ከማለትና 'ተነሥተህ ሂድ' ከማለት የቱ ይቀልላል? ነገር ግን የሰው ልጅ በምድር ላይ ኀጢአትን የማስተሰረይ ሥልጣን እንዳለው እንድታውቁ ነው" ብሎ፣ ሽባውን፣ "ተነሣ! ቃሬዛህን ይዘህ ወደ ቤትህ ሂድ" አለው። ሽባውም ተነሥቶ ወደ ቤቱ ሄደ»።*

**ኢየሱስ አምላክ መሆኑን አረጋግጧል።** ኢየሱስ ስለ ልደቱ፣ ህይወቱ እና ሞቱ የተነገሩትን የብሉይ ኪዳን ትንቢቶችን በሙሉ ፈፅሟል። አምላክ መሆኑን ለማሳየት በርካታ ተአምራትን አድርጓል። በስልጣን አስተማሯል። *«ኢየሱስ ማስተማሩን በፈጸመ ጊዜ፣ ሕዝቡ በትምህርቱ ተደነቁ። 29ምክንያቱም እንደ አይሁድ ሃይማኖት መምህራናቸው ሳይሆን እንደ ባለሥልጣን ያስተምራቸው ስለ ነበር ነው።»* ማቴዎስ 7፥28-29። ኢየሱስ ኃጢአት የሌለበት ሕይወትም ኖረ፣ ዕብ 4፥15፣ 1ኛ ጴጥሮስ 2፥22፣ 1ኛ ዮሐንስ 3፥5። ኢየሱስ፣ ኃጢአት የሌለበት ፍፁም አምላክ-ሰው ነውና፣ ስለ ኃጢአታችን በመስቀል ላይ የተሰዋ ፍጹም የእግዚአብሔር በግ ሆነ። *«ለኀጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር እርሱ ራሱ በሥጋው ኀጢአታችንን በዕንጨት መስቀል ላይ ተሸከመ፤ በርሱ ቍስል እናንተ ተፈውሳችኋል።»* 1ኛ ጴጥሮስ 2፥24።

**ኢየሱስ ተሰቀለ፣ ሞተ እናም ከሞት ተነሳ።** *«ከቀድሞ አባቶቻችሁ ከወረሳችሁት ከንቱ ከሆነ ሕይወት የተዋጃችሁት በሚጠፋ ነገር፣ በብር ወይም በወርቅ እንዳልሆነ ታውቃላችሁ፤ ነገር ግን እናንተ የተዋጃችሁት ነውርና እንከን እንደሌለበት በግ ደም፣ በክርስቶስ ክቡር ደም ነው።»* 1ኛ ጴጥሮስ 1፥18-19። ደግሞም ሰዎች እርሱን በዕንጨት ላይ ሰቅለው ገደሉት። *«እግዚአብሔር ግን በሦስተኛው ቀን ከሙታን አስነሣው፤ እንዲታይም አደረገው፤ ...በርሱም የሚያምን ሁሉ በስሙ የኀጢአትን ስርየት እንደሚቀበል ነቢያት ሁሉ ይመሰክሩለታል።»* ሐዋ 10፥39-40፣43። *«እኔ የተቀበልሁትንና ከሁሉ በላይ የሆነውን ለእናንተ አስተላልፌአለሁ፤ ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚሉት ክርስቶስ ስለ ኀጢአታችን ሞተ፤ ተቀበረ፤ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ተጻፈውም በሦስተኛው ቀን ተነሣ፤»* 1ኛ ቆሮንቶስ 15፥3-4 ኢየሱስ ከሞት ተነስቶ ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት በብዙ ምስክሮች ታይቷል።

**ወደ እግዚአብሔር የሚወስደው መንገድ ኢየሱስ ብቻ ነው።** ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ *«መንገዱ እኔ ነኝ፤ እውነትና ሕይወትም እኔው ነኝ፤ በእኔ በኩል ካልሆነ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።»* ዮሐ 14፥6 ሐዋርያው ጴጥሮስ እንዲህ ብሏል፣ *«ድነት በሌላ በማንም አይገኝም፤ እንድንበት ዘንድ ለሰዎች የተሰጠ ከዚህ ስም በቀር ሌላ ስም ከሰማይ በታች የለምና።»* ሐዋ 4፥12። ሐዋርያ ዮሃንስ እንዲህ ሲል ፅፏል፣ *«አንድ እግዚአብሔር አለና፤ ደግሞም በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል አንድ መካከለኛ አለ፤ እርሱም ሰው የሆነው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤ ራሱንም ለሰዎች ሁሉ ቤዛ አድርጎ ሰጠ፤ ይህም በትክክለኛው ጊዜ ተመስክሮለታል።»* 1ኛ ጢሞቴዎስ 2፥5-6። ኢየሱስ ወደ እግዚአብሔር የሚወስደው መንገድ መሆኑ ከሌሎች ሃይማኖቶች ሁሉ የተለየ ያደርገዋል። ሌሎች ሃይማኖቶች ለኃጢአታችን ችግራችን መፍትሄ አይሰጡንም። በአጠቃላይ ሃይማኖቶች እንደ ጥሩ እና መጥፎ ፍቺያቸው መልካም ብታደርግ አማልክቶቻቸው ኃጢአትህን ሽረውልህ ወደ መንግሥተ ሰማያት እንድትገባ ሊፈቅዱልህ እንደሚችሉ ያስተምራሉ። የኢየሱስ መንገድ በእርሱ በማመን ለኃጢያትህ ዋጋ በመስቀል ላይ የተከፈለበት እና ይቅር የተባለበት ነው። ኢየሱስን በማመን ይቅር ተብለህ ወደ መንግሥተ ሰማያት ትገባለህ። *«በርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስከ መስጠት ድረስ ዓለምን እንዲሁ ወድዷልና።»* ዮሐንስ 3፥16።

**ኢየሱስ ይመለሳል።** ኢየሱስ እንዲህ አለ፡- *«ልባችሁ አይጨነቅ፤ በእግዚአብሔር እመኑ፤ በእኔም ደግሞ እመኑ። በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፤ ይህ ባይሆንማ ኖሮ እነግራችሁ ነበር፤ የምሄደውም ስፍራ ላዘጋጅላችሁ ነው። ሄጄም ስፍራ ካዘጋጀሁላችሁ በኋላ፣ እኔ ባለሁበት እናንተም ከእኔ ጋራ እንድትሆኑ ልወስዳችሁ ዳግመኛ እመጣለሁ።»* ዮሐንስ 14፥2-3። ኢየሱስ በመጽሐፍ ቅዱስ የመጨረሻ ቃላቶች ላይ እንዲህ ብሏል፣ *«እነዚህን ነገሮች የሚመሰክረው፣ "አዎ፣ ቶሎ እመጣለሁ" ይላል።»* ሐዋርያ ዮሃንስ ጨምሮ፣ *«አሜን፤ ጌታ ኢየሱስ ሆይ፤ ና»* ራዕይ 22፥20-21። ኢየሱስ ዛሬ ቢመጣ እሱን ለማግኘት ዝግጁ ነህን? በኢየሱስ በማመን እና በእግዚአብሔር ይቅርታ በማግኘት ዝግጁ መሆንህን ለማረጋገጥwww.Gospel316.orgን ጎብኝ።

**ኢየሱስ ከዘላለም እስከ ለዘላለም አምላክ ነው።**

**በስሙ መጠራቱ ተዓምር በመደነቅ እጅግ ተገረሙ!**

*ኢየሱስ ማን ነው?* © 2025 በ John D. Morris III በ Acts One Eight ታትሟል። ይህን ሙሉ መግለጫ በማያያዝ ይዘቱን ሳትለውጥ በነጻ ማተም፣ መቅዳት፣ መለጠፍ፣ ኢሜይል ማድረግ ወይም መልእክት መላክ ትችላለህ። የአገልግሎትህን ወይም የቤተ-ክርስቲያንህን ስም ወይም አርማ በገጽ አንድ ላይ ማከል እና የእውቂያ መረጃህን ከገጽ ሁለት ግርጌ አጠገብ ካለው ጠንካራ መስመር በላይ መፃፍ ትችላለህ። Jesus316 የተመሰረተው በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ብቻ ነው። አላማውም ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ እንዲያምኑና የእርሱ ደቀ መዛሙርት እንዲሆኑ ለመርዳት ነው። Acts One Eightን (ከተቻለ በእንግሊዝኛ) ወደሚከተለው ኢሜይል መላክ ትችላለህ፡- Hello@Mail316.org. በእንግሊዝኛ ቋንቋ ያልተዘጋጁ ስራቶች የትርጉም አገልግሎቶች በ www.ChristianLingua.com ላይ ቀርበዋል። *ኢየሱስ ማን ነው?* www.Jesus316.org ላይ በ48 ቋንቋዎች በነጻ ይገኛል። በእንግሊዝኛው እትም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት ከሎክማን ፋውንዴሽን አዲሱ የአሜሪካ መደበኛ መጽሐፍ ቅዱስ 1995 ነው። በዚህ ትርጉም ላይ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት ከአዲሱ መደበኛ ትርጉም ነው።